ቁጥር/Ref.No/TI/6042/CWD/2018

Date/ቀን/:- ህዳር 19/2018ዓ.ም.

የአካባቢ ግልጽ ጨረታ

ኩባንያችን ጢስ እሳት ዉኃ ስራዎች ኃ/የተ/የግ/ማህበር በምስራቅ ጎጃም ዞን በአማኑኤል ወረዳ እየገነባ ለሚገኘው ለአማኑኤል የገጠር ሽግግር ማዕከል መጠጥ ውሃ ፕሮጀክት፣ በአዊ ዞን በባንጃ ወረዳ እየገነባ ለሚገኘው ለአርዲ አነስተኛ ደረጃ መስኖ ፕሮጀክት እና በደቡብ ጎንደር ዞን በፋርጣ ወረዳ እየተገነባ ለሚገኘው ለመገናኛ መስኖ ፕሮጀክት ከተለያዩ ተቋማት ጋር ውል በመውሰድ የግንባታ ስራዎችን እያከናወነ ሲሆን ውል ከወሰደባቸው የስራ ገዘርገዘር ውስጥ የጉልበት ስራ በዘርፉ ለተሰማሩና ደረጃ - 4 እና ከዚያ በላይ WC እና GC በሆኑ የንዑስ ተቋራጮች ማሰራት ይፈልጋል፡፡

1. ንዑስ ተጫራቾች ለዘመኑ የታደሰ የብቃት ማረጋገጫ ሰነድ፣ የንግድ ፈቃድ፣ የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት፣ የተጨማሪ እሴት ታክስና የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር /TIN/ ሰርተፊኬት እንዲሁም የታክስ ክሊራንስ ማስረጃዎች ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡
2. ንዑስ ተጫራቾች የመስሪያ ዋጋቸውን ሲሞሉ ለስራው የሚያስፈልግ ማንኛውም የሰው ሀይል ወጪን ያካተተ እንደሆነ ታሳቢ ማድረግ ይኖርባቸዋ፡፡
3. ንዑስ ተጫራቾች የጨረታ ሰነዱን በባህር ዳር ከተማ፣ አጼ ቲወድሮስ ክፍለ ክተማ፣ ማራኪ ቀበሌ፣ ቴዲ የአሸከርካሪዎች ማሰልጠኛ ተቋም ፊት ለፊት ከሚገኘው የኩባንያው ዋና መ/ቤት ቢሮ ቁጥር 010 /የኮንትራት አስተዳደርና ገበያ ልማት መምሪያ/ በነጻ (ያለ ክፍያ) መዉሰድ ይችላሉ፡፡
4. ጨረታው ይህ የጨረታ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ከህዳር 19/2018 ዓ.ም. ጀምሮና ቅዳሜን ጨምሮ ለ07 ተከታታይ የስራ ቀናት ብቻ አየር ላይ የሚቆይ ሲሆን በ7ኛው ቀን ከቀኑ 9:00 ሰዓት ጨረታው ተዘግቶ በዚሁ ቀን ከቀኑ 9:30 ሰዓት ባህር ዳር ከተማ፣ አጼ ቲወድሮስ ክፍለ ክተማ፣ ማራኪ ቀበሌ፣ ቴዲ የአሸከርካሪዎች ማሰልጠኛ ተቋም ፊት ለፊት በሚገኘው የኩባንያው ዋና መ/ቤት ተጫራቾች ወይም ሕጋዊ ወኪሎች በተገኙበት ይከፈታል፡፡
5. የጨረታው መገዢያና መክፈቻ ቀን የስራ ቀን ካልሆነ ጨረታው በሚቀጥለው የሥራ ቀን በተመሳሳይ ሰዓት ተዘግቶ ይከፈታል፡፡
6. ስለጨረታው በጽሁፍም ሆነ በስልክ ማብራሪያ /ክላሪፊኬሽን/ መጠየቅ ይቻላል፡፡
7. ንዑስ ተጫራቾች የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና ለሚያቀርቡት የመስሪያ ዋጋ የተጨማሪ እሴት ታክስን ጨምሮ 1% ተቀባይነት ያለው የጨረታ ማስከበርያ ዋስትና (Bid Bond) በባንክ የተረጋገጠ የክፍያ ትዕዛዝ (CPO)፣ በሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ የባንክ ዋስትና (Unconditional Bank Guarantee) ወይም በጥሬ ገንዘብ ማስያዝ ይኖርባቸዋል፡፡

Scanned by CamScanner

8. ተጫራቾች በጨረታ መወዳደሪያ ሰነዱ /Bid document/ መሰረት የቴክኒካል ሰነዳቸውን፣ ዋጋ ማቅረቢያቸዉን እና የጨረታ ማስከበሪያቸዉን በታሸገ ፖስታ እና የድርጂቱን ስም በማስቀመጥና ማህተም በመምታት ማቅረብ ይኖርባቸዋል።
9. ንዑስ ተጫራች ድርጅቶች በሚያቀርቡት የመስሪያ ዋጋ ላይ ለእያንዳንዱ ስራ ነጠላ ዋጋ እና ጠቅላላ ዋጋውን በማያሻማ ሁኔታ በትክክል በእጅ ጽሁፍ መሙላት አለባቸው።
10. በሚቀርበው የቴክኒካልና የመስሪያ ዋጋ ማቅረቢያ ሰነዶች ላይ የድርጅቱ ሕጋዊ ተወካይ ፊርማና የድርጅቱ ማህተም ሊይኖርበት ይገባል።
11. ንዑስ ተጫራቾች የሚያቀርቡት የመስሪያ ዋጋ የግንባታ አቃምችን ከዋናው ተቋራጭ መጋዘን ተሸከርካሪ ላይ መጫንም ሆነ ማውረድ ስራ፣ በሰው ሀይል ማጓጓዝ፣ መገንቢያ፣ የገርጋታና የሌሎች ወጭዎችን የሚሸፍን ይሆናል። ሌሎች ከስራዎች ጋር የተያያዙ የጉልበት ወጪዎች በተሰጠው ዋጋ ላይ ተጠቃለው መቅረብ ይኖርባቸዋል። ይህ ገርዘር የሚገልጸው ከአማኑኤል የገጠር ሽግግር ማዕከል መጠጥ ውሃ ፕሮጀክት (ሎት-2) ላይ ከተገለጸው ስራ ውጭ ላሉት ስራዎች ብቻ ይሆናል።
12. የጨረታዉ አሸናፊ አሸናፊነቱ በጽሁፍ ከተገለጸበት ቀን ጀምሮ ባሉት ተከታታይ 5 ቀናት ውስጥ የተጨማሪ እሴት ታክስን ጨምሮ የጠቅላላ መስሪያ ዋጋዉን 10% በሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ የባንክ ዋስትና (Unconditional Bank Guarantee) ወይም 30% በኢንሹራንስ የተዘጋጀ ዋስትና የዉል ማስከበሪያ በማቅረብ ዉል የመያገዝ ግዴታ ይኖርበታል።
13. ስራውን ሰርቶ የማጠናቀቂያ ጊዜ የግንባታ ቦታ ርክክብ ከተደረገበት ቀን ጀምሮ የሚየገዝ ሲሆን ለአማኑኤል የገጠር ሽግግር ማዕከል መጠጥ ውሃ ፕሮጀክት 6 ወር፣ ለአርዲ አነስተኛ ደረጃ መስኖ ፕሮጀክት 4 ወር እና ለመገናኛ መስኖ ፕሮጀክት 4ወር ጊዜ ውስጥ መሆን አለበት።
14. ንዑስ ተጫራቾች በጨረታ ወቅት የሚያቀርቡት ዋጋ ጨረታው ከተከፈተበት ቀን ጀምሮ ውል እስከሚያገበት ቀን ቢያንስ ለ30 ቀናት ፀንቶ መቆየት የሚችል መሆን አለበት።
15. ሥራውን በገባው ውል መሠረት ያላከናወነ ንዑስ ተቋራጭ ለእያንዳንዱ የዘገየበት የግንባታ ቀናት የውሉን ጠቅላላ ዋጋ 0.1% በየቀኑ በቅጣት መልክ ይከፍላል። ነገር ግን የጉዳት ካሳ ቅጣቱ ከ10% በላይ መብለጥ የለበትም።
16. ለአማኑኤል የገጠር ሽግግር ማዕከል መጠጥ ውሃ ፕሮጀክት (ሎት-2) ቅድመ ክፍያ የውሉን ጠቅላላ መጠን 20% ሲሆን በሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ 20% የባንክ የቅድመ ክፍያ ዋስትና ሲቀርብ በሁለት ዙር የሚከፈል ይሆናል። ይህም የመጀመሪያ 10% ቅድመ ክፍያ ስራ ተቋራጩ የሳይት ርክክብ በአደረገ በ7 ቀናት ውስጥ የሚከፈል ሲሆን የሁለተኛው ዙር 10% ቅድመ ክፍያ ደግሞ ወደ ስራ ከገቡ በኋላ ተፈፃሚ ይሆናል። ተጫራቾች ለዚህ ስራ የሚያቀርቡት ዋጋ አስፈላጊውን ማሽነሪ፣ ተሽከርካሪ እና ሌሎች ለስራው አስፈላጊ የሆኑ ኢኩፕመንቶችን ያካተተ መሆን አለበት።
17. ከላይ በተራ ቁጥር 16 ለተጠቀሰው ስራ 5% ለዋስትና ማስከበሪያ ከክፍያ ላይ የሚቀነስ ይሆናል።

Scanned by CamScanner

18. ይህ የአካባቢ ግዥ ግልፅ ጨረታ የውል አካል ሆኖ ይወሰዳል።
19. ጨረታው ከተከፈተ በኃላ ንዑስ ተጫራቾች ባቀረቡት የመወዳደሪያ ሃሳብ ላይ ለውጥ ወይም ማሻሻያ ማድረግና ከጨረታው ራሳቸውን ማግለል አይችሉም።
20. አንድ ንዑስ ተጫራች ኩባንያው በሚያወጣው ጨረታ ላይ ከ2 (ሁለት) ፕሮጀክት በላይ መሳተፍ አይችልም።
21. ጨረታው ሲከፈት የጨረታውን ሃደት ለማዛባት የሚሞክሩ ንዑስ ተጫራቾች ከጨረታው ውጭ ይሆናሉ። ለወደፊቱም ድርጅቱ በሚያደርጋቸው ሌሎች ጨረታዎች ላይ አይሳተፉም። ያስያዙት የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትናም ይወረሳል።
22. ኩባንያው የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው። ለበለጠ መረጃ በስልክ ቁጥራችን 058-220-48-26/ በፋክስ ቁጥራችን 058-220-48-30 መጠየቅ ይችላሉ።

ኩባንያው

Scanned by CamScanner